መመሪያ-ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS (MCPS)
ሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅነት ያላቸው ደንቦች፡- ACA፣ ACF፣ ACF-RA፣ IHC-RA፣ IJA-RA፣ IOE-RB፣ ISB-RA፣ JEA-RA፣ JEC-RA፣ JEG-RA፣ JHB-RA፣ JHE-RA

ኃላፊ ጽ/ቤት፡- ዋና የአካደሚ መኮንን

እርግዝና ላይ ላሉ እና ልጅ ለሚያሳድጉ ተማሪዎች ትምህርት ስለሚቀጥሉበት ሁኔታ መመሪያ

I. ዓላማ

በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) እርግዝና ያላቸው እና ልጅ የሚያሳድጉ ተማሪዎችን የፌደራል እና የስቴት ህግ ትግበራ/አፈጻጸም ጋር የሚጣጣም ኃላፊነት ለመስጠት እርጉዝ እና ልጅ የሚያሳድጉ ተማሪዎችን በት/ቤት ለማቆየት የሚችሉበትን ሁኔታ የመርዳት ቅደም-ተከተሎችን ለመንደፍ።

II. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. እርጉዝ ወይም ልጅ የሚያሳድጉ ተማሪዎች ላይ መድልዎን ወይም ጾታዊ ጥቃትን/ትንኮሳን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች፡-

1. የፌደራል ህግ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ፀረ መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና ባህልን ማዳበር/ባህላዊ ብቃት፣ እና የቦርድ ፖሊሲ ACF፣ ጾታዊ ጥቃት/ትንኮሳ፣ የእርግዝና እና የወላጅነት/አራስነት አቋምን ጨምሮ በትምህርታዊ መርሃግብሮች እና እንቅስቃሴዎች ላይ በጾታ ምክንያት መድልዎን ወይም ጥቃትን/ትንኮሳን መከልከል።

a) በተማሪ የእርግዝና ወይም የወላጅነት አቋም ምክንያት ት/ቤቶች ተማሪን በማናቸውም ክፍል ወይም በከፊል የትምህርት ፕሮግራም፣ እንደ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ ከፍ ያለ ደረጃ ምደባ፣ ወይም የላቀ የትምህርት ክፍሎች፣ ከከሪኩለም ውጭ የሚሰጡ ፕሮግራሞች፣ በት/ቤቶች መካከል በሚካሄዱ የስፖርት ውድድሮች፣ በኦነር ሶሳይቲ፣ ወይም ለተማሪ የመሪነት/የሊደርሽፕ እድሎች መሣተፍን ለመከልከል አይችሉም።

b) ት/ቤቶች ከ እርግዝና ወይም ልጅ ከማሳደግ/ወላጅነት ጋር በተዛመደ ለአካላዊ እና ስሜታዊ ሁኔታ ሲባል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዳይሳተፉ፣ማድረግ ካስፈለገ ሌሎች ተማሪዎች እንዳይሳተፉ በሚፈቅዱበት ተመሳሳይ ሁኔታ ብቻ እንዳይሳተፉ መፍቀድ ይኖርባቸዋል።

c) ት/ቤቶች ከጤና ባለሙያ ማስረጃ ሠነድ መፈለግ ያለባቸው እርጉዝ ወይም ወላጅ ተማሪ በክፍል እና ከቀለም ትምህርት ውጪ በሆኑ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ከሌሎች በአካላዊ ወይም ስሜታዊ ሁኔታ በህክምና ላይ ከሚገኙ ተማሪዎችም ከጤና ባለሙያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ ከሆነ ብቻ ነው።

d) ለእርጉዝ ተማሪ የትምህርት ፕሮግራም ማመቻቸትን አስመልክቶ፣ አስፈላጊ ሲሆን፣ ት/ቤት በመደበኛው ፕሮግራም ላይ ተገቢ እና የተማሪን የእርግዝና ሁኔታ ግምት ውስጥ

በማስገባት (ለምሳሌ፡- ት/ቤቱ ተለቅ ያለ ዴስክ መስጠት ይኖርበት ይሆናል፣ ወደ መፀዳጃ ክፍል ቶሎ ቶሎ መመላለስ ካስፈለገ መፍቀድ፣ ወይም ኤሌቬተር ለመጠቀም ጊዜያዊ ፈቃድ መስጠት) ጊዜያዊ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልጋል።

2. ጾታዊ ጥቃት ወይም ከጾታዊነት ጋር የተገናኘ ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር አድሎአዊነትን ወይም ከእርግዝና ወይም ወላጅነት ጋር የተገናኘ ማስፈራራትን ጨምሮ ጉዳዩ ላይ ትኩረት እንዲደረግበት ለሚሹ ተማሪዎች የት/ቤት አስተዳደር ኮምፕሊያንስ ክፍል ጽ/ቤት ከት/ቤት ሠራተኞች ጋር በመተባበር መመሪያ፣ እና/ወይም ከጎን የመቆም/እንደ ጠበቃዋ የመሆን ድጋፍ ይሰጣል።

B. ማማከር

1. መምህራን ወይም ሌሎች ሠራተኞች እርጉዝ ወይም ወላጅ ተማሪ መኖሩን ካወቁ ወይም ይሆናል ብለው የሚያምኑበት ምክንያት ካላቸው ለት/ቤት ካውንስለር፣ ለት/ቤት ማህበረሰብ ነርስ (SCHN)፣ ለት/ቤት የጤና ቴክኒሻን፣ ወይም ለርእሰ መምህር/ተወካይ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

2. እርጉዝ ወይም ልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪ እርግዝና በምስጢር እንዲያዝ ሠራተኞቹን ከጠየቁ፣ ሠራተኞቹ በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

   a) የት/ቤት ካውንስለርን፣ ወይም SCHN አገልግሎቶችን ለመጠቀም እንድትችል ተማሪን ማደፋፈርና መርዳት ያስፈልጋል፣ እናም

   b) በዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ ከወላጅ/ሞግዚት ጋር የሚደረግ ማንኛውም አይነት ግንኙነት መደረግ ያለበት ከት/ቤት ካውንስለር እና/ወይም ከርእሰ መምህር እንዲህ ዓይነት ኢንፎርሜሽን ሚስጥራዊ መሆኑን እና ወደ ሌሎች ተማሪዎች የማይደርስ መሆኑን ለማረጋገጥ በመመካከር መሆን አለበት።

3. ከሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ IJA-RA ጋር የሚጣጣሙ የት/ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች፣ የት/ቤት ካውንስሊንግ ፕሮግራሞች

   a) በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙትን ድጋፍ ሰጪ አካላትን ለይተው እንዲያውቁና ተገቢ የሆኑ ማህበራዊ አገልግሎቶችን እና የጤና እንክብካቤ መገልገያዎችን/resources የመጠቀም እድሉን እንዲወስዱ ተማሪን ያማክራሉ።

   b) በአካዳሚክ መሥኮች፣ በሥራ፣ ጤንነት፣ ከሰዎች ጋር እና በግል እድገት ለእርጉዝ/ለነፍሰጡር ወይም ልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪዎች ፍላጎት ምላሽ መስጠት፣

   c) ለእርጉዝ ወይም ልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪ ያሉትን የአካደሚ አማራጭ እድሎችን መዳሰስና ያሉትን ድጋፎችን ለማስፋት/ለማሳደግ ከጎን መቆም/ማቀንቀን እነዚህም የሚያካትቱት ክሬዲት ማሻሻል፣ የግል ጥናት፣ ሁለትዮሽ ምዝገባ፣ ከፊል ጊዜ መማር/መከታተል፣ ወይም የትምህርት ግስጋሴአቸውን ለመጠበቅ ሌሎች የትምህርት አማራጮችን መስጠት፣ እና

   d) የመመረቂያ እቅድን ለማዳበር ከእርጉዝ ወይም ከልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪ ጋር መሥራት።

4. በተጨማሪም፣ በእርግዝና ምክንያት ወይም በወሊድ ምክንያት ትምህርት ያመለጣቸው ተማሪዎች በጤንነት ሁኔታ ምክንያት ትምህርት ቤት ለመምጣት ካልቻሉ እንደሌሎቹ የሞንትጎመሪ ካውንቲ

ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በአንድ ዓይነት መልክ ጊዜያዊ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል።

5. SCHN፣ የት/ቤት የጤና ቴክኒሻን፣ ርእሰ መምህር/ት ወይም ተወካይ፣ እና/ወይም አግባብነት ያለው የት/ቤት ካውንስለር፣ እንደየአግባቡ ለእርጉዝ ወይም ወላጅ ለሆነች ተማሪ ስለ... ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

   a) በፌደራል ህግ መሠረት ያላቸው መብት፣ እና

   b) በማህበረሰብ ኤጀንሲዎች እና በአጋሮች የሚሰጡ ማህበራዊ አገልግሎቶች እና የጤና እንክብካቤ ድጋፎችን ጨምሮ መገልገያዎች ይኖራሉ።

C. የትምህርት ክትትል እና ማካካሻ - ሥራ

1. ተማሪ በርግዝና ወይም በወላጅነት ፍላጎት ምክንያት ከት/ቤት መቅረት በፌደራል እና በስቴት ህግ መሠረት በ MCPS ደንብ JEA-RA ላይ እንደተገለጸው ህጋዊ መቅረት ነው። የተማሪ ትምህርት መከታተል

2. ከዚህ በላይ በስትራተጂ II.B ላይ ከተገለጸው በተጨማሪ፣ እርጉዝ ወይም ልጅ አሳዳጊ ወላጅ ተማሪ ከቀሩበት ቀናት ጋር አቻ ለሆነ የጊዜ ገደብ ያመለጠን ትምህርት ለማካካስ እንዲቻል እንደ አግባቡ ተማሪን ወደ አማራጮች መምራት እና የሚከተሉትን ያካተተ ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፡-

   a) ሴሚስተሩን እንደገና መማር

   b) በድረገጽ ክሬዲት ማሻሻያ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ

   c) ተማሪው(ዋ) በያዘው/በያዘችው እርምጃ እንዲቀጥል/እንድትቀጥል እና ዘግይቶ/ዘግይታ እንዲጨርስ/እንድትጨርስ መፍቀድ።

D. ትምህርት ማቋረጥ

ተማሪ በእርግዝና ወቅት ወይም በወላጅነት ምክንያት ትምህርት ለማቋረጥ ብትፈልግ፣ ለ .. የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች ማናቸውንም ጥረት ማድረግ አለባቸው።

1. ከት/ቤት የማቋረጥ አስተያየት ከመሰጠቱ አስቀድሞ ተፈላጊ የኮርስ ማስተካከያዎች እንዲያደርጉ ተማሪዎችን መርዳት ያስፈልጋል።

2. ከተማሪ፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የተማሪው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ፣ አቀንቃኞች፣ መምህራን፣ ካውንስለሮች፣ የተማሪ ሥራ ሠራተኞች እና የአስተዳደር ሠራተኞች እንደአስፈላጊነቱ፣ የተማሪን ችግር ለማቅለል የታለመ በችግሩ ሁኔታ ላይ ያተኮረ ስብሰባ ማድረግ፣

3. MCPS ቅጽ 565-4a በመሙላት የትምህርት ቃለመጠይቅ ማድረግ፣ ትምህርት ማቋረጥን ለመከላከል የታለመ ትምህርታዊ ቃለመጠይቅ፣እንደሁኔታው እንደ አግባብነቱ እና

4. ትምህርት ማቋረጥን ለመከላከል ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎችንና ዶኩመንቴሽንም መከተል በ MCPS ቅጽ JEC-RA ላይ እንደተገለጸው ተማሪ ከመማሪያ ክፍሎች እና ከት/ቤት ማቋረጥ

ተዛማጅነት ያላቸው ምንጮች፡- Title IX of the *Education Amendments Act of 1972,* as amended; Annotated Code of Maryland, Education Article, §7-301.1; U.S. Department of Education Office of Civil Rights "Know Your Rights:/ሙብትሽን/ሙብትህን ማወቅ እርጉዝ ወይም ወላጅ/Pregnant or Parenting? Title IX በትምህርት ቤት አድሎ እንዳይደረግ ይከላከላል" እና "በ Title IX of the Education Amendments of 1972" ድንጋጌ መሠረት እርጉዝ ተማሪዎችንና ወላጅ ተማሪዎችን በአካደሚክ ስኬታማ እንዲሆኑ መርዳት

ስለ ደንቡ ታሪክ፡- ቀደም ሲል Regulation No 335-6, ኤፕሪል/April 12, 1977 ይባል ነበር፣ ዲሴምበር 1986 ተሻሽሏል፣ ጃኑወሪ 22፣ 1996 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 26፣ 2006 ተሻሽሏል፣ፌብሩወሪ 26፣ 2018 ተሻሽሏል። ቴክኒካዊ ማሻሻያ የተደረገው ሴፕቴምበር 25/2018 ነው።